የሚጠይቅ ህብረተሰብና ጋዜጠኛ አገራችን ውስጥ የለም ወይ? ለነኝህ ጥያቄዎች የሚኖረውን ምላሽ ለታሪክና ለሕዝብ እንተዋለን።

ዛሬ ለኢዴአፓ-መድህን ወሳኙ ጥያቄ የትናንትናውን ሕመም ከማስታመም በላይ በተስፋ መቁረጥ ስሜት እየተናደ የሚገኘውን የኢትዮጵያን ሕዝብ የለውጥ ምኞትና ተስፋ እንደገና መገንባት ነው። የፓርቲያችን ዋነኛ ዓላማ በአገራችን የተረጋጋ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲመሠረት፣ የሕዝቦች ሁለንተናዊ መብቶች እንዲረጋገጡ ማድረግ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፍትህንና ሁለንተናዊ ብልፅግናን ማረጋገጥ ነው። እንደ ፓርቲያችን እምነት ወደዚህ ግብ እስከምንደርስ ድረስ ከፊት ለፊታችን ያሉ የግድም መታለፍ ያለባቸው ችግሮች አሁንም ፈታኝና ውስብስብ ናቸው። ገና ፓርቲያችን ሲመሰረት እንደተነተነው የዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብ እጥረት በህብረተሰባችን ውስጥ ስር የሰደደ ነው። ገዥው ፓርቲ እና ተቃዋሚዎችም ሁላችንም የዚህ ህብረተሰብ ውጤቶች እንደመሆናችን መጠን ከችግሩ ነፃ አይደለንም። በዚች አገር እውነተኛ ስርዓት ለማረጋገጥ አሁንም ትግላችን በህብረተሰባችን ውስጥ ስር ከሰደዱ ፀረ-ዲሞክራሲያዊ አስተሳሰቦችና እምነቶች፣ ከገዥው ፓርቲ የአምባገነንነት ባህሪና እንዲሁም የገዥውን ፓርቲ መታገልን ለራሳቸው የዲሞክራሲያዊነት ብቸኛ ማረጋገጫ ካደረጉ ፀረ-ዲሞክራሲ አስተሳሰብ ካላቸው የተቃዋሚ ኃይሎች ጋር ጭምር ነው።

በአሁኑ ወቅት በበርካታ የተቃውሞ ፖለቲካ አራማጅ ወገኖች መካከል የሚታየው የአገሪቱን ብሔራዊ ጥቅምና ክብር እንዲሁም አንድነቷንና ዘላቂ ሕልውናዋን የሚፃረር የፖለቲካ አካሄድ ኢዴአፓ-መድህንን በብርቱ ያሳስበዋል። ይህ ከፖለቲካ ብቃት ማነስ የመነጨ ደካማነት ብቻ ሳይሆን የቅንነት እጦትም ጭምር መሆኑን ኢዴአፓ-መድህን ሲገነዘብ ቆይቷል። እንዲህ አይነት የፖለቲካ ደካማነትና ቅንነት ማጣት የኢትዮጵያን ችግሮች ያባብስ እንደሆነ እንጂ በምንም መሥፈርት በአገራችን የለውጥ ተስፋ እውን ሊያደርግ አይችልም። በእነኝህ ኃይሎች ጭፍን ቅስቀሳ ምክንያት ዛሬ በኅብረተሰባችን ውስጥ እየተንፀባረቀ የሚገኘው ስሜታዊነት አገራችንንና ሕዝባችንን ይበልጥ ይጐዳ እንደሆነ እንጂ ከቶውንም እንደማይጠቅም ግልፅ ነው።

ባለፉት ሁለት ዓመታት ፓርቲያችን በከባድ ፈተና ውስጥም ሆኖ ራሱን ለዚህ ፈተና የዳረጉ ችግሮችንና የወደፊት አቅጣጫውን ለማሰብ በቂ ጊዜ አግኝቷል። በኢትዮጵያ ተቃውሞ ፖለቲካ ውስጥ ሥር የሰደዱ ችግሮችንም ለመፈተሽ ሞክሯል። ለትግሉ መሳካት ሕዝቡ ከፍተኛ መስዋዕትነት ከከፈለ በኋላ የአመራር ድክመትና የተጠና ስልታዊ አስተሳሰብ እጦት በትግሉ ላይ ከፍተኛ ሽንፈትና ውድቀት ማስከተሉን አረጋግጧል። ዛሬ በተቃዋሚው ጐራ ውስጥ ከዚህ ሽንፈትና ውድቀት የመነጨ ተራ የእልኸኝነትና የጭፍን ጥላቻ አስተሳሰብ የሰፈነ መሆኑንም አረጋግጧል። ይህ አሁንም ትግሉን ለበለጠ ጉዳት በመዳረግ የአገሪቱን እጣ ፋንታ የሚያወሳስብ መሆኑን አስምሮበታል። ስለሆነም ራሱን ከዚህ አላቅቆ በመርህ ላይ በተመሠረተና ምክንያታዊ በሆነ ፖለቲካዊ መንገድ ብቻ ለመራመድ ወስኗል። በዚች አገር ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት እውን ሊሆን የሚችለው በሰላማዊና ዲሞክረሲያዊ መንገድ ብቻ እንደሆነ የነበረውን እምነት የበለጠ በማጠናከር ለዚህም ግብ ረጅምና ያልተቋረጠ ትግል ለማካሄድ የነበረውን አቋሙን አፅንቷል። በርካታ ተቃዋሚ ኃይሎች ባለፉት ዓመታት እንዴት ኢህአዴግን በተቻለ ፍጥነት ከሥልጣን አስወግደን ሥልጣን እንይዛለን በሚል ቁንፅል አላማ ላይ ብቻ አትኩረው ከመጡበትና አሁንም እየሄዱ ከሚገኙበት መንገድ አንፃር ኢዴአፓ-መድህን እራሱን በተለየ ሁኔታ በማየት በኢትዮጵያ ለሚካሄደው የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ትግል ከሌሎች ተቃዋሚዎችና ከገዥው ፓርቲ በተለየ የሦስተኛ አማራጭነትን መንገድ ይከተላል።

ባለፉት ዓመታት በተቃውሞ ትግሉ ጐራ የኢዴአፓ-መድህን አባልና ደጋፊ ሆናችሁ እስከ ግንቦት 97 ምርጫ ድረስ የቆያችሁና ከምርጫው በኋላ በፓርቲያችን ዙሪያ በተፈጠሩ የአሉባልታ ዘመቻዎችና እነዚህን ተከትሎ በተፈጠረ ውዥንብር መነሻነት ከፓርቲያችን የራቃችሁ አንዳንድ የፓርቲያችን አባሎች ስለፓርቲያችን እስካሁን ድረስ የተወራው አሉባልታ ሁሉ ሆን ተብሎ የፓርቲያችንን ጥሩ ስምና ዝና ለማጥፋት የተቀነባበረ ጥቃትና ተራ ውሸት መሆኑን ተረድታችሁ ታጋይነታችሁንና የፓርቲ አባልነታችሁን በማደስ ወደ ትግሉ እንድትመለሱ ኢዴአፓ-መድህን ጥሪ ያቀርባል። የተቃውሞ ትግሉን በተለያዩ መንገዶች ስትደግፉ የነበራችሁ ሁሉ በትግሉ ላይ ካለፈው ምርጫ በኋላ ያየነው አስከፊ ውድቀት የደረሰው በኢዴአፓ-መድህን መነሻነት ሳይሆን በሌሎች ስህተትና ጥፋት መሆኑን ከዛሬ ደርሰን ጊዜ እየመሰከረልን ካለው በላይ እኛ ልንናገር አንሻምና በፓርቲያችን ላይ የነበራችሁን እምነት በማደስ ከጐናችን እንድትሰለፉ ኢዴአፓ-መድህን ጥሪ ያቀርባል!



☎ 0115-508727 0114655765 ✉ 101458
0115-508728
ፍልውሃ ቅርንጫፍ የባንክ ሂሳብ ቁጥር A/C 145